ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ። በናንተ ውስጥ የመርየም ልጅ ፍትሃዊ ዳኛ በቅርቡ ሆኖ ይወርዳል። መስቀልን ይሰባብራል፣ አሳማን ይገድላል፣ ግብርን ያነሳል፣ አንድም ሰው እስከማይቀበለው ድረስም ገንዘብ (ሀብት) ይበዛል።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ። በናንተ ውስጥ የመርየም ልጅ ፍትሃዊ
ዳኛ በቅርቡ ሆኖ ይወርዳል። መስቀልን ይሰባብራል፣ አሳማን ይገድላል፣ ግብርን ያነሳል፣ አንድም ሰው እስከማይቀበለው ድረስም
ገንዘብ (ሀብት) ይበዛል።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የመርየም ልጅ ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በሰዎች መካከል በነቢያችን ድንጋጌ በፍትህ ሊፈርዱ መውረጃ ጊዜያቸው ቅርብ እንደሆነ ምለው ተናገሩ። በሚመጡ ወቅትም ክርስቲያኖች የሚያልቁትን መስቀል ይሰባብራሉ፤ ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አሳማዎችንም ይገድላሉ፤ ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ግብርንም ያስቀራሉ፤ ሰዎች ባጠቃላይ ወደ ኢስላም እንዲገቡም ይታገላሉ፤ ገንዘብ (ሀብት) ይትረፈረፋል አንዱ ከሌላው አይቀበለውም። ይህም ገንዘብ ከመብዛቱ፣ ሁሉም እያንዳንዱ እርሱ ዘንድ ባለው ገንዘብ የተብቃቃ ከመሆኑ፣ በረካ ሰፍኖ መልካምነትም ከመከታተሉ አኳያ ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/65025